የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 54
ADDIS ABABA- 30th June. 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፬/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ ገጽ ፫ሺ፩፻፸፩

CONTENTS

Proclamation No. 464/2005

Protection of Telecommunications and Electric Power Networks Proclamation Page 3171

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፬/፲፱፻፺፯

## የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ

ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ለማምጣት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ወሳኝ ሚና ያላቸው በመሆኑና እነዚህንም ለማስፋፋት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ሚጠይቅ በመሆኑ፣

የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮች በመላ ሀገሪቱ ተሰራጭው የሚገኙ ሲሆን በባሕሪያቸው ለጥቃት ድርጊት የተጋለጡ በመሆናቸውና አገልግሎቶቹ ለአፍታ እንኳ ቢቋረጡ በብሔራዊ ኢኮኖሚና ደህንነት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እጅግ ከፈተኛ በመሆኑ፣

የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮች ከብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት አንጻር የተለየ የሕግ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፬/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 464/2005.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PROTECTION OF TELECOMMUNICATION AND ELECTRIC POWER NETWORKS

**WHEREAS,** telecommunications services and electric power supply play pivotal role in bringing about rapid economic and social development and at the same time expansions of the sectors require huge investments;

**WHEREAS,** the telecommunication and electric power networks are expanded all over the country and the sectors by their very nature are exposed for illegal acts and the interruption of the services, even for a while, will bring damage to the national economy and security of the country;

**WHEREAS,** the national interest and security requires special protection for telecommunications and electric power networks;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Protection of Telecommunications and Electric Power Networks Proclamation No. 464/2005".

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "የቴሌኮመኒኬሽን አውታር" ማለት ከቴሌኮሙኒኬሽን ሲስተመ ጋር በተያያዘ አገልግሎት ላይ የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማናቸውም መሣሪያ፣ የመሣሪያው ተገጣሚ አካል፣ ሳተላይት፣ ኦፕቲካል ፋይበር፣ ታወር፣ ማስት፣ አንቴና፣ ሽቦ፣ ኬብል፣ ምሰሶ ወይም ማናቸውም እስትራክቸር ነው፣

፪/ "የኤሌክትሪክ ኃይል አውታር" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨትና ማስተላለፍ ሲስተም ጋር በተያያዘ አገልግሎት ላይ የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማናቸውም መሣሪያ፣ የመሣሪያው ተገጣሚ አከል፣ ሽቦ፣ ኬብል፣ ምሰሶ ወይም ማናቸውም እስትራክቸር ነው፣

፫/ "የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት በሕግ የተቋቋመና ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ፈቃድ አውጥቶ የቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ የሚሠራ ሰው ነው፣

፬/ "የኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ድርጅት" ማለት በሕግ የተቋቋመና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኤጀንሲ ፈቃድ አውጥቶ የኢሌክትሪክ ኃይል የማቅረብ ሥራ የሚሠራ ሰው ነው፣

፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

## ፫. ጥበቃ

፩/ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አውታሮች በዚህ አዋጅ መሠረት የተለየ ጥበቃ ተሰጥቷቸዋል፣

፪/ በየደረጃው ያሉ የፌደራልና የክልል አስተዳደር አካላት ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት እና ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ድርጅት ጋር በመተባበር በመላ ሀገሪቱ የተዘረጉ የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፣

፫/ ማንኛውም ፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳደር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት በአካባቢው የቴሌሙኒኬሽን ወይም ኤሌክትሪክ ኃይል አውታር ስለመኖሩ እና ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሙኬሽን ወይም በኤሌክትሪክ አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው::

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "telecommunication networks" means any equipment or accessories thereof, satellite, optical fiber, wire, cable, tower, mast, antenna, pole or any structure used or intended to be used in connection with telecommunications system;

2/ "electric power network" means any equipment or accessories thereof, wire, cable, pole or any structure used or intended to be used in connection with electric power generation and transmission system;

3/ "telecommunications service provider" means a telecommunications operator established by law and having license from the Ethiopian Telecommunication Agency;

4/ "electric power supplier" means an electric power supplier established by law and having license from the Ethiopian Electric Agency;

5/ "person" means a natural or juridical person

## 3. Protection

1/ Telecommunications and electric power networks all over the country are hereby provided special protection by this Proclamation.

2/ Any federal and regional administrative body shall, in collaboration with the telecommunication service provider and electric power supplier, have the duty to protect telecommunications and electric power networks.

3/ Any federal and regional city administrative body shall ensure whether there are telecommunications or electric power networks prior to issuance of construction license and any person who acquired license, shall also guarantee that no damage shall occur on telecommunications or electric power networks.

## ፬. ቅ ጣ ት

የሀገር ደህንነትን ወይም ኢኮኖሚን በሚጎዳ ሁኔታ በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌክትሪክ አውታር ላይ የስርቆት ተግባር የፈፀመ ወይም ሆነ ብሎ ጉዳት ያደረሰ ወይም አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ያደረገ ማንኛውም ሰው፣ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የበለጠ የሚቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ ከ፭ እስከ ፳ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል:: የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልኝነት ከሆነ ቅጣቱ ከ፮ ወር እስከ ፭ ዓመት የሚደርስ እስራት ይሆናል::

## ፭. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

## ፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 4. Penalties

Any person who has committed an act of theft or intentional destruction or obstruction of telecommunications or electric power networks, which threaten the national security and economy of the country, shall, unless a higher penalty is applicable under the relevant provisions of the Criminal Code, be punishable with rigorous imprisonment from 5 to 20 years. Where such act is committed negligently the punishment shall be from 6 months to 5 years imprisonment.

## 5. Inapplicable laws

Any law inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters provided for by this Proclamation.

## 6. Effective Date

The Proclamation shall enter into force on the 30th day of June, 2005.

**Done at Addis Ababa, the30th day of June, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**